# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 336 ጥቅምት 8 2007


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ጥቂት የህወሓት ጥጋበኞች በብዙሃኑ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚያደርሱት በደል ማብቃት አለበት ይላል። ግንቦት 7፡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት በሙስና የደለቡት፣ ትዕቢተኛና ጨካኝ መሪዎቻቸው ፍጹም ኢትዮጵያዊ ባህርይ የሌላቸው ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች እንደሆኑ በመረዳት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ክንዱን እንዲያነሳባቸው ጥሪ ያደርጋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአሜሪካ ሲያትል ዋሽንግተን ዉስጥ የተሳካ ህዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

የግንቦት 7 ንቅናቄ ቅዳሜ ኦክቶበር 11 ቀን 2014 ኢ.ም በአሜሪካ ሲያትል ከተማ ደማቅ ህዝባዊ ስብሰባ ማካሄዱን ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል። በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ በሲያትልና አጎራባች ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በነቂስ በመውጣት የታደሙበት እንደነበር ያደረሰን ዘጋቢያችን አገር ወዳድ ኢትዮጵያኑ በስብሰባው ላይ በክብር እንግድነት ከተገኙት የንቅናቄው ሊቀመንበር ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር ሰፊ አገራዊ ውይይት ማካሄዳቸውን ለማወቅ ተችሏል። በሲያትል የተካሄደው ይህ ህዝባዊ ስብሰባ ኢትዮጵያውያን በዘር በሃይማኖት በጎሳ ሳይለያዩ በአንድነት በመሰባሰብ በአገራቸው ጉዳይ ላይ በሰፊው የመከሩበት፤ ኢትዮጵያዊነት እጅግ አምሮና አሸብርቆ የታየበት እንደነበርም ተመልክቷል።

በህዝባዊ ስብሰባው ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት ዶ/ር ብርሀኑ ለስብሰባው ታዳሚዎች ባደረጉት ንግግር “የምንገኝበት ወቅት ጊዜያችንን እንደ ከዚህ ቀደሙ መቋጫ በሌለው ውይይትና ጭቅጭቅ የምናጠፋበት ሳይሆን፤ ስለ ነፃነቴ እታገላለሁ የሚል ወደ ተግባራዊው ትግል የሚቀላቀልበት፤ በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ትግሉን መቀላቀል የፈራ ዝም ሊል የሚገባበት ወቅት መሆኑን በአንክሮ በማስገንዘብ በተጨማሪ የነፃነት ትግሉን በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳ የሚገኘውን የእርስ በርስ ጥልና ሽኩቻ በአስቸኳይ ቆሞ ሁላችንም በአንድነት በመነሳት በዋናው አላማችን ላይ ማለትም የጉጅሌው ወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ መዝመት ይገባናል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል። በተለይ የነፃነት ትግሉ ለመቀላቀል እስካሁን እድሉን ላላገኙና በትግሉ ላይ የራሳቸው የታሪክ አሻራ ማሳረፍ ለሚሹ ወገኖችም የተቀላቀሉን ጥር ማቅረባቸውን ለማወቅ ተችሏል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በደቡብ ክልል ቤንች ማጅ ዞን ጦረነት መቀስቀሱ ታወቀ

በቤንች ማጅ ዞን የፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ጦር ከመዠንግር ታጣቂዎች ጋር የጀመረው ግጭት ወደ ከፍተኛ ደም አፋሳሽ ጦርነት መለወጡን ዘጋቢያችን ከአካባቢው ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። በእስካሁኑ ጦርነት ቁጥራቸው ከ 60 በላይ የሆኑ የአገዛዙ ቅጥረኛ ወታደሮች እንዲሁም ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የመዠንግር ጎሳ ታጣቂዎች መገደላቸውን ለማወቅ ተችሏል። ጦርነቱ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤ መፈጠሩንም ለማወቅ ተችሏል። የመዠንግር ታጣቂዎች ያልተጠበቀ ጥቃት በአገዛዙ ቅጥረኛ ጦር ላይ ማድረሳቸውን ተከትሎ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የገባው ፋሽስቱ ወያኔ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦርና ከባድ መሳሪያዎችን ጭምር ወደ አካባቢው ማንቀሳቀሱ ታውቋል። ጦርነቱ እጅግ በጣም እየተካረረ መሄዱን ያደረሰን የአካባቢው ዘጋቢያች በሁለቱም ወገን ከፍተኛ እልቂትና የንብረት ውድመት ሊያስከትል እንደሚችል ጠቁሟል። አድማጮቻችን እየተካሄደ ያለውን ጦርነት በተመለከተ ዝርዝር መረጃው እንደደረሰን በሐሙሱ ፕሮግራማችን የምናቀርብ መሆኑን ከወዲሁ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በተያያዘ ዜና በደቡብ ክልል በጉራፈርዳ ወረዳ ዳግም የተቀሰቀሰው ለዘመናት የኖሩ የአካባቢው ነዋሪዎችን የማፈናቀል እንቅስቃሴ ወደ ግጭት መለወጡ ታውቋል። በእስካሁኑ ግጭት ቁጥራቸው ከ 30 በላይ ሰዎች መገደላቸውን እንዲሁም በርካታ ነዋሪዎች ለዘመናት የኖሩበትን ቀያቸውን በመልቀቅ ነፍሴ አውጭኝ ሽሽት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱ ወደ አስከፊ ደረጃ መለወጡን ተከትሎ ከፍተኛ ጥቃት እየተፈጸመባቸው የሚገኙት ተፈናቃዩች የድረሱልን ጥሪ እያሰሙ እንደሚገኙም ታውቋል። ፋሽስቱ ወያኔ እየተከተለ ያለው የገለማ የዘር ፖለቲካ ለግጭቱ ዋናው መንስኤ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ከቅርብ አመታት ወዲህ የአገዛዙ ሹማምንቶችና ቅጥርኛ ባለሃብቶች በአካባቢው እያደረሱ የሚገኙት ከፍተኛ የመሬት ቅርምት ለግጭቱ መባባስ አስተዋጽኦ ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል።

## በቤንች ማጅ ዞን በተቀሰቀሰው ጦርነት ከ 115 በላይ ዜጎች ተገደሉ፤ ጦርነቱ ከፍተኛ ንብረት እያወደመ ነዉ

የፋሽስቱ ወያኔ የዘር ፖለቲካ ውጤት እንደሆነ በስፋት የተነገረለትና ባሳለፍነው ሳምንት የተጀመረው በቤንች ማጅ ዞን በሸኮና መዠንግር ጎሳ ታጣቂዎች እና በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ጦር መካከል የተቀሰቀሰው ደም አፋሳሽ ጦርነት በእስካሁኑ በሁለቱም ወገን ከ 115 በላይ ሰዎችን ህይወት መቅጠፉንና ከ 50 በላይ ቤቶችን ለቃጠሎ በመዳረግ ከፍተኛ የንብረት ውድመት አስከትሎ መቀጠሉን የአካባቢው ተባባሪ ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። ከሟቾቹ ውስጥ ከ 43 በላይ የሚሆኑት የአገዛዙ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች፤ እንዲሁም 18 ቱ ደግሞ ቅጥረኛ ወታደሮች መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። በጦርነቱ የተገደሉት የአገዛዙ ቅጥረኞ ወታደሮች አስከሬን በሚዛን አማን ሆስፒታል እንዲገባ ከተደረገ በኋላ፣ ዘመድ ያላቸው ወደ ዘመዶቻቸው ሲሸኙ፣ የቀሪዎቹ የቀብር ስነስርዓት ደግሞ ሚዛን ውስጥ መፈጸሙን ለማወቅ ተችሎአል። ይሁን እንጂ በጦርነቱ የተገደሉት የሸኮ እና መዠንገር ጎሳ ታጣቂዎች አስከሬን እየተከታተለ የሚለቅም ባለመኖሩ ለረጅም ሰአታት በየ ሜዳው ወዳድቀው መታየታቸውን የአይን እማኞች አመልክተዋል። ጥቂት የማይባሉ የጎሳዎቹ ታጣቂ አስከሬኖች አሁንም ድረስ በየ ጥሻው ወዳድቀው እንደሚገኙ አያይዞ ያደረሰን ዘጋቢያችን ግማሽ አካላቸው በጅብ ተበልቶ የተገኙ አስከሬኖች መኖራቸውንም ለማወቅ ተችሏል። ወረዳዋ አሁንም ድረስ የጦር አውድማ ሆና በተኩስ እየተኛጠች መቀጠሏ የተመለከተ ሲሆን የሸኮና መዠንግር ጎሳ ታጣቂዎች በአገዛዙ በኩል እያደረሱት ያለው ከፍተኛ ጥቃት ምን አልባትም ፋሽስቱ ወያኔን ወደ ዘር ማጥፋት ወንጀል ሊያመራው ይችላል የሚል ስጋት ማየሉ ተመልክቷል። በተለይ ከሳለፍነው ማክሰኞ ጀምሮ በአካባቢው እየተሰማ ያለው የከባድ መሳሪያ እሩምታ የወረዳውን ህዝብ ከፍተኛ ሽብር እና ጭንቀት ውስጥ ከቶት እንደሚገኝም ተባባሪ ዘጋቢያችን ገልጿል። ጦርነቱ እጅግ ረጅም ጊዜን ሊወስድ ይችላል የሚል ስጋት በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ አይሎ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜና የሸኮ መዠንገር ተወላጆች ታጣቂዎች በሚዛን ከተማና በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች ጭምር በመሄድ በአካባቢው ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የዘረኞች ፍርድ ቤት ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን ጥፋተኛ ነህ ብሎ ኮነነ

ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሀይልና በአመፅ እንዲፈርስና አመፅ እንዲቀሰቀስ ተንቀሳቅሃል በሚል የፈጠራ ክስ ተከሶ ላለፉት ሁለት አመታት በጉጅሌው ወያኔ የካንጋሮ ፍርድ ቤት ሲመላለስ የነበረው እውቁ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን በመጨረሻ የካንጋሮው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሲል የመወሰነበት መሆኑንና ወደ ወህኒ መውረዱን ለማወቅ ተችሏል። የጉጅሌው ወያኔ በአገዳት በቀድሞው “ፍትህ” ጋዜጣው ላይ “መጅሊሱ፣ ሲኖዶሱና የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ማጥመቂያዎች”፣ “የፈራ ይመለስ” እና “የብሄረሰቦች መብት እስከ መጨፈር” በሚሉ ርእሶች በተለያዩ ጊዜያት በወጡት ፅሁፎች፤ አገዛዙን በአመፅ ለመናድ ቀስቅሷል፣ የአገዛዙን ስም አጥፍቷል፣ የህዝብን አስተሳሰብ ለማናወጥ ሰርቷል፤ የሚሉ መሰረት የለሽና የፈጠራ ክሶች በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ተለጥፈውበት በካንጋሮው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሲያስተባብል መክረሙ ይታወሳል። የጥፋተኝነት ውሳኔ በማሳለፍ ወደ ወህኒ ቤት የተወሰደ ጋዜጠኛ ተመስገን ለቅጣት ውሳኔ ለጥቅምት 17 ተቀጥሯል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉጅሌው ወያኔ የካንጋሮ ፍርድ ቤት ያሳለፈው ወሳኔ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ማስቆጣቱ ታውቋል። ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የተወሰደበትን ህገ ወጥ የእስር እርምጃ አስመልክቶ ሲናገር «ለእስረኛ ማልቀስ/ ማዘን ሳይሆን የእስረኛውን መንገድ መከተል ነው፡፡ የእስር መብዛት ወደፊት፣ ነገ ላይ በሀገራችን የሚያመጣው ለውጥ አለ፡፡» በማለት መልዕክቱን ለኢትዮጵያ ህዝብ መላኩን ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜና በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ መሰረት የለሽ የፈጠራ ክስ ተለጥፎባቸው ለእስር ተዳረገው በካንጋሮው ፍርድ ቤት ጉዳያቸው እየታየላቸው የሚገኙት የዞን 9 ጦማርያን እና ጋዜጠኞች ዳግም ፍርድ ቤት ቢቀርቡም የካንጋሮው ፍርድ ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ለጥቅምት 25 በመስጠት አሰናብቷቸዋል። የጉጅሌው ወያኔ አገዛዙን ይተቻሉ የሚላቸውን ጋዜጠኞችን፤ ብሎገሮችንና ጸሃፊዎች በማሰሩና በማሰደዱ አለማቀፍ ትችት እያስተናገደ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ይህ ህገወጥ እርምጃው አገዛዙን ከአፍሪካ ግንባር ቀደም አምባገነኖች ተርታ አሰልፎት እንደሚገኝ የተለያዩ አለማቀፍ መንግስታትና ተቋማት ምስክርነታቸውን እየሰጡ ይገኛሉ። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ካውንስል ዘረኛው ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሕዝብ ወገንተኝነቱን የሚያሳይበት  ወቅት አሁን ነው!

ዘረኛውና ፋሽስታዊው የህወሓት አገዛዝ የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት በዘርና በፓለቲካ ወገንተኝነት በመከፋፈል ሹመቱና ጥቅማ ጥቅሙን ለራሱ ወገን፣ ችግሩንና መከራዉን ግን ለሌላው ኢትዮጵያዊ ያደለ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት ሳይማሩና ሳይሰለጥኑ የጄኔራልነት ማዕረጎችን በሙሉ ሰብስበው የወሰዱት የህወሓት አባላት መሆናቸው የአደባባይ ሚስጢር ነው።

በወያኔ መዳፍ ውስጥ እየተሰቃየች ባለችው ኢትዮጵያችን ውስጥ በዘርም ይሁን በፓለቲካ አመለካከት ከህወሓት የተለዩ ኢትዮጵያዊያን ቢማሩም ቢሰለጥኑም ለከፍተኛ አመራርነት እንደማይበቁ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ያየነው ነው። አገዛዙ ቅራኔ ውስጥ በገባባቸው ቦታ ሁሉ እየዘመቱ ሕይወታቸውን እየገበሩ ያሉት ግን በመካከለኛና ዝቅተኛ ማዕረጎች ያሉ ኢትዮጵያዊያን መኮንኖችና ብዙሃኑ የሠራዊቱ አባላት የሆኑ ወታደሮችናቸው። ብዙሃኑ የሠራዊት ክፍል አለቆቹን ከመጠበቅ ባለፈ ድምጹን ከፍ አድርጎ ለመናገር እንኳን  የማይፈቀድለት ሎሌ ተደርጓል።

ለኢትዮጵያዊ ወታደር ለህወሓት ሎሌ ከመሆን በላይ የሞት ሞት የለም። ብዙሃኑ የኢትዮጵያ መከላከያ  ሠራዊቱ አባላት በጥቂት የወያኔ ሹማምንት የሚረገጥ መሆኑ የሠራዊቱን አባላት የግል ስብዕና ብቻ  ሳይሆን በአጠቃላይ የሠራዊቱን ክብር ይነካል። የሠራዊታችን የህወሓት አገልጋይ መሆን የምንወዳት አገራችን ኢትዮጵያን ያዋርዳል። ይህ ዉርደት በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለበትም።

ከእንግዲህ ጄኔራሎችና ሌሎችም የበላይ አዛዦች ሁሉ የአንድ አካባቢ ተወላጆች በሆኑበት ሠራዊት ውስጥ ተስማምቶ መኖር መቀጠል እያንዳንዱን የመከላከያ ሠራዊት አባል ሊያሰፍር ይገባል። የህወሓት ጄኔራሎች ጮማ በውስኪ ሲያወራርዱ፤ በህንፃዎች ግንባታ፣ በባንኮች ንግድ፣ በግብርናና በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሰማርተው ቢዝነሳቸውን ሲያጧጥፉ፣ ምስኪኖቹ የሠራዊቱ አባላት በኦጋዴን፣ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በአማራና በሌሎች የአገሪቱ ግዛቶች እየተወረወሩ ወገኖቻቸውን የሚፈጁበት ሥርዓት ማብቃት አለበት።  የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ብዙሃኑ አባላት ቤተሰቦቻቸው በችጋር እየተቆሉ የአዛዦቻቸው ሀብት ጠባቂ መሆናቸው ማክተም አለበት።

የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የጭለማ ዘመን ታሪክ እያበቃ መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች እየታዩ ነው። መሣሪያዎቻቸውን እንደያዙ የነፃነት ኃይሎችን የሚቀላቀሉ የሠራዊቱ አባላት ቁጥር ከጊዜ  ወደጊዜ እየጨረመ መጥቷል። ሠራዊቱ ከሕዝብ ጎን እንደሚቆም ውስጥ ውስጡን የሚላኩ መልዕክቶች እየተበራከቱ መጥተዋል። ይህ አበረታች ዜና ነው፤ ግን በቂ አይደለም። ወያኔን ከውስጥም ከውጭም የምናጣድፍበት ጊዜው አሁን ነው። የነፃነት ኃይሎችን መቀላቀያ  ጊዜ አሁን ነው፤ በሠራዊቱ ውስጥም በህቡዕ መደራጃ ጊዜ አሁን ነው። ይህን ጊዜ መጠቀም ብልህነት ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ጥቂት የህወሓት ጥጋበኞች በብዙሃኑ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚያደርሱት በደል ማብቃት አለበት ይላል። ግንቦት 7፡ የኢትዮጵያ መከላከያ  ሠራዊት አባላት በሙስና የደለቡት፣ ትዕቢተኛና ጨካኝ መሪዎቻቸው ፍጹም ኢትዮጵያዊ ባህርይ የሌላቸው ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች እንደሆኑ በመረዳት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ክንዱን እንዲያነሳባቸው ጥሪ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሕዝብም የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አንድ ወጥ እንዳልሆነ እና በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ያሉ መኮንኖችና አብዛኞዎቹ ወታደሮች የሕዝብ ወገን መሆናቸውን እንዲገነዘብ ያሳስባል። “አብረን ነው ዘረኛውና ፋሽስቱን ወያኔን ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ አውርደን  የምንጥለው” ስንል አብዛኛው የመከላከያ ሠራዊታችን ኢትዮጵያዊ ወገናችን እንደሆነ እና በወደፊቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ውስጥም ጉልህ ሚና  እንዲጫወት የምንፈልግ መሆኑን ግልጽ ማድረግ እንሻለን። የመከላከያ ሠራዊቱም የሕዝብ ወገንተኝነቱ በተግባር እንዲያሳይ ጥሪ እናደርጋለን። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የሕዝብ አካል ነው፤ የሕዝብ ወገናዊነቱ በተግባር የሚያሳይበት ትክክለኛ ጊዜ ደግሞ  አሁን ነው እንላለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

---

## የአሜሪካ ኤምባሲ አልሸባብ በአዲስ አበባ ጥቃት ሊፈጽም እንደሚችል አስጠነቀቀ

አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ አልሸባብ የተባለዉ የሽብርተኞች ድርጅት ቦሌ አዉሮፕላን ማረፊያ አካባቢ ጥቃት ለመፈጸም በዝግጅት ላይ ለመሆኑ መረጃ አለኝ ሲል አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ዜጎቹን አስጠነቀቀ። ኤምባሲው አዲስ መግለጫ እስከሚወጣ ድረስ ዜጎቹ ከሆቴሎች፣ ምግብ ቤቶች፣ የማምለኪያ ቦታዎች፣ ከገበያ ቦታዎችና የመዝናኛ ቦታዎች እንዲርቁ መክሯል። ጥቃቱ የሚፈጸምበት  ትክክለኛ ቦታ ባይታወቅም ፣ የአሜሪካ ዜጎች የራሳቸውን ደህንነት እንዲጠብቁ አሳስቧል።

የኢትዮጵያ መንግስት በበኩሉ የአልሸባብን ዛቻ እንደሚያከሽፈው ገልጿል።የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት መረጃዎችን ይፋ ያደረገው ዊኪለኪስ ከአመታት በፊት የኢትዮጵያ መንግስት “በአገሪቱ የሽብር አደጋ አለ ለማለት ፈንጅዎችን እንደሚያቀናብር” ይፋ አድርጎ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ካለፉት 9 አመታት ጀምሮ በሶማሊያ ውስጥ ከዩጋንዳ፣ ብሩንዲና ኬንያ ሰራዊት ጋር በጥምረት ከአልሸባብ ጋር እየተዋጋ ቢሆንም፣ እስካሁን አልተሳካለትም። አልሸባብ በእነዚህ ሃይሎች ጥቃት ከሞቃዲሾና ዋና ዋና ከሚባሉ ስትራቴጂያዊ ቦታዎች እንዲለቅ ተገዷል።

## በአዋሽ ወንዝ ሙላት ከ87 በላይ ሰዎች ሲሞቱ ከ500 በላይ ሰዎች ደብዛቸው ጠፋ

አፋር ክልል ዉስጥ የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ ከ87 በላይ የአካባቢ ነዋሪዎችን መግደሉንና ከ500 በላይ ሰዎች  ደግሞ የደረሱበት አለመታወቁን በክልሉ የሚገኙት ምንጫቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የወያኔ መሪዎች እንደለመዱት የወንዙ መሙላት በሰዉ ህይወት ላይ ምንም አይነት ጉዳት አላደረሰም ብለዉ የዋሹ ሲሆን ይህንን አይን ያወጣ ዉሸት ሰመዶቻቸዉና ቤተሰቦቻቸዉ የሞቱባቸዉ የአካባቢዉ ነዋሪዎች አጥብቀዉ አዉግዘዋል። የሞቱብንን 87 ሰዎች ቀብረናል ያሉት ኗሪዎች የአደጋዉ ዜና  የተነገረው ጉዳት ከደረሰ ከሳምንት በኃላ መሆኑንና  እርዳታም የደረሰዉ ብዙ ነገረ ከወደመ  በሁዋላ በመሆኑ ችግሩን የከፋ አደርጎታል ሲሉ በምሬትና በቁጣ ተናግረዋል።

በድርጊቱ እጅግ ማዘናቸውን የገለጹት ነዋሪዎች ተቆርቋሪ መንግስት የለንም በሚል ወቀሳ አቅርበዋል። ችግሩ አሁንም አስከፊ በሆነ ሁኔታ መቀጠሉን በመግለጽ ቀይ መስቀል እንዲድረስላቸው ተማጽነዋል።

የአዋሽ ሙላትን በተመለከተ ኢሳት ከሁለት ቀን በፊት ባቀረበው ዘገባ ነዋሪዎች የሞቱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ብለው መገመታቸውን ገልጸ ነበር።

---

## ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአሜሪካ ሲያትል ዋሽንግተን ዉስጥ የተሳካ ህዝባዊ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የቀረበላቸውን ጥሪ በመጠቀም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ኢትዮጵያውያን በአባልነት እንዲሁም በደጋፊነት በመመዝገብ ግንቦት 7 ትን መቀላቀል መቻላቸው ታውቋል። ትግሉ አሁን ላይ የደረሰበትን ደረጃ አስመልክቶ ለታዳሚዎች በስፋት ያብራሩት ዶ/ር ብርሃኑ ተሰብሳቢዎቹ እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7 ለነደፋቸው የትግል ስልቶች ማለትም ለሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት እና ሕዝባዊ አመጽ ዛሬ ነገ ሳይባል ምላሽ መስጠት መጀመር እንዳለበት ማሳሰብያ ማቅረቡ ታውቋል። በተለይ እነዚህን ስልቶች በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ በተቀናጀ ሁኔታ መተገበር በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቆም ብሎ ሊያስብና ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሊገባ የሚገባበት ሰአት አሁን ነው ያሉት ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን በተሳካ ሁኔታ መተግበር ስንችል ጉጅሌዎቹን ከአገራችንንና ከህዝባችን ጫንቃ ማውረድ እንችላለን ሲሉ ተናግረዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ ከተሰብሳቢው ለቀረበላቸው በርካታ ጥያቄዎችም አጥጋቢ ምላሽ ሰጥተዋል። በተለይ በኤርትራ በኩል እየተደረገ ያለውን ትግል አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሰፊ ምላሽና ማብራሪያ በመስጠት በተሰብሳቢዎች ዘንድ የነበረውን ብዥታ ማጥራት መቻላቸውንና ተሰብሳቢዎቹ እየተደረገ ላለው ትግል በጭብጨባ ድጋፍ መስጠታቸውን ከስፍረሰው  የደረሰን መረጃ አመልክቷል።

በመጨረሻም በስብሰባው ላይ በጠላት እጅ ወድቀው የሚገኙት የንቅናቄያችን ዋና ፀሐፊ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሥራዎች በስፋት መወሳታቸውን ለማውቅ የተቻለ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑ የአቶ አንዳርጋቸው ስራዎች ሲቀርቡ አብዛኞቹ በሐዘን እና በቁጭት ሲያነቡ እንደነበርም የደረሰን መረጃ ያመለክታል። በስብሰባው መገባደጃ ላይ ለጨረታ የቀረበው የነፃነት አርበኛው የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ፎቶግራፍም በከፍተኛ ገንዘብ መሸጡ ታውቋል። ኢትዮጵያውያኑ በጋራ እጅ ለእጅ በመያያዝ እየተደረገ ያለውን የነፃነት ትግል ከዳር ለማድረስ ከመቼውም ጊዜ በላይ በቁርጠኝነት መነሳታቸውን በቃለ መሐላ ካረጋገጡ በኋላ ስብሰባው መፈጸሙም ታውቋል።

---

## “እኔ ብቻ” ቢያክሙት የማይሽር የወያኔ በሽታ

ዘረኝነት፤ ጎጠኝነትና ዕብሪት የወያኔ አዲሰ ባህሪያት ሳይሆኑ አስራ ሰባት አመት ጫካ ዉስጥ በቆየባቸዉ አመታትና ዛሬም ከጫካ ወጥቶ አገር እየመራ በቆየባቸዉ ሃያ ሦስት አመታት አብረዉት የኖሩ መታወቂያ ካርዶቹ ናቸዉ። ዘረኝነት፤ አማራ ጥላቻና የትግራይ ሪፓብሊክ ህልም ዋና ዋናዎቹን የወያኔ መሪዎች ደደቢት በረሃ ከገቡ በኋላ በድንገት የለከፋቸዉ በሽታ ሳይሆን ከና ከልጅነታቸዉ ተጠናዉቷቸዉ አብሯቸዉ ያደገ በሽታ ነዉ። ወያኔ ጨካኝ ነዉ፤ ወያኔ ዉሸታም ነዉ፤ወያኔ ከሃዲ ነዉ፤ ወያኔ ለኢትዮጵያ ዳርድንበርና የግዛት አንድነት ደንታ የሌለዉ ባዕድ አካል ነዉ። እነዚህ ሁሉ የወያኔን ማንነትና ምንነት በትክክል የሚገልጹ የወያኔ በሽታዎች ናቸዉ። በዛሬዉ ቆይታችን በልዩ መነጽር አብረን የምንመለከተዉ የወያኔ በሽታ ግን በአይነቱ ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት በሽታዎቸ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በጠባይና በአገላለጽ ግን ለየት ያለ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለአመታት እንዳየዉም ሆነ ህወሓትን መስረተዉ ለስልጣን ያበቁትና ህወሓት ለእነሱም አልበጅ ብሏቸዉ ጥለዉት የወጡት ግለሰቦች በቃልም በጽሁፍም እንደነገሩን ወያኔ የጫካ ዉስጥ ጠባዩን ዛሬም ያልለቀቀ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ዛሬማ ጭራሽ ብሶበት ያየዉን ነገር ሁሉ ነጥቆ የራሱ ካላደረገዉ ወይም ሙሉ ለሙሉ ካልተቆጣጠረዉ አርፎ የማይተኛ ድርጅት ሆኗል። ብዙዎቻችን የወያኔ ስም በተነሳ ቁጥር ትዝ የሚለን ዘረኝነቱ ነዉ። በእርግጥም ወያኔ ግለሰብንና ግለሰቦችን ወይም የተለያዩ ቡድኖችን በዘር መነጽር ብቻ የሚመለከት ዘረኛ ድርጅት ነዉ። ሆኖም ወያኔንና ወያኔ የፈጠረዉን ዘረኛ ስርዐት ለመደምሰስ የሚደረገዉ ትግል የወያኔን ዘረኛ ገጽታ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የወያኔ ገጽታዎች ማጋለጥና መዋጋት አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ ወያኔ በፕሮፓጋንዳዉ ይዋጋናል፤ በዲፕሎማሲ ዘርፍ ይዋጋናል፤ በማህበራዊ ሜዲያዉ ዘርፍ ለተሳዳቢዎች ገንዘብ እየከፈለ ይዋጋናል፤ ከዚህ በተጨማሪ በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸዉ ፍርድ ቤቶች፤ ፖሊስ፤ መከላከያና የደህንነት ተቋሞች አማካይነትም ይዋጋናል። አዎ ! ወያኔ በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸዉ ተቋሞች አማካይነት እንቅልፉን ትቶ ቀንና ማታ ይዋጋናል። ዉድ አድማጮቻችን እቺን ወያኔ በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸዉ ተቋሞች አማካይነት ይዋጋናል የምትለዋን አባባል ጠበቅ ያደረግነዉ አለምክንያት አይደለም። ዛሬ ብዙ የምናወራዉ ስለዚሁ “ሁሉን ነገር መቆጣጠር” ስለሚለዉ የወያኔ አባዜ ነዉ።

በወያኔ የበላይነት የተጻፈዉ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት - የኢትዮጵያ ብሄር፤ ብሄረሰቦች፤ ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸዉ ይላል። ሆኖም የዚህ ሉዓላዊነት መገለጫ በሆነዉ ፓርላማ ዉስጥ 38 መቀመጫዎች ብቻ ያለዉ ህወሓት 509 መቀመጫዎች ያላቸዉን ከትግራይ ዉጭ ያሉትን ሌሎቹን የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የፖለቲካ ህይወት ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል። የሚገርመዉ ወያኔ የሚቆጣጠረዉ የኢትዮጵያን ህዝብ የፖለቲካ ህይወት ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያን የኤኮኖሚና የማህበራዊ ዘርፎችም ሙሉ በሙሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር የወደቁ ናቸዉ። በአጠቃላይ ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ በዬትኛዉም ዘርፍ ከላይ እስከታች እሱ የማይቆጣጠረዉ ምንም ነገር እንዲኖር አይፈለግም። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ዉሰጥ በወያኔና በሁለቱ ግዙፍ የአገራችን ሐይማኖቶች መካከል ለአመታት የዘለቀዉ ንትርክ፤ አተካሮና ፍጥጫም የዚሁ የወያኔ ሁሉንም ነገር እኔ ብቻ ካልተቆጣጠርኩት የሚል ክፉ አባዜ ዉጤት ነዉ።

የወያኔ “እኔ ብቻ” አባዜ አዲስ አበባ ገብቶ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የተጀመረ አዲስ እብደት ሳይሆን ወያኔ ገና በረሃ ዉስጥ እያለም ሰፊዉን የትግራይ ጫካ እኔ ብቻ ካልተቆጣጠርኩት የሚል በሽተኛ ድርጅት ነበር። ይህ ደግሞ ወያኔን ስለምንቃወመዉ ብቻ የምንለዉ ተራ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን ወያኔን ፈጥረዉ ለዛሬዉ ሥልጣን ካበቁትና ዛሬ የወያኔ አካሄድ አንገሽግሿቸዉ ይህንን ድርጅት በአይናችን አናይም ብለዉ ከማሉ የትግራይ ተወላጆች አንደበት የወጣ ሐቅ ነዉ። እነዚህ የወያኔን ታሪክ የተረኩልን ወይም በመጽሐፍ ጽፈዉ ያስነበቡን ግለሰቦች ወያኔ አንዳንድ እንደነሱ ጫካ ገብተዉ ትግል የጀመሩ የትግራይ ድርጅት መሪዎችን ለስብሰባ ጠርቶ ማታ በተኙበት ቦታ አንገታቸዉን እንዳረደ ሳይደብቁ ነግረዉናል። ወያኔ የትግራይን ጫካና በረሃ ብቻዬን ካልተቆጣጠርኩ በሚል ከኢዲህና ከኢህአፓ ጋር በተከታታይ ደም የተቃባ ድርጅት ነዉ። በተለይ ኢህአፓዎችን የትግራይ መሬት የናንተ አይደለምና ለቅቃችሁ ካልወጣችሁ እያለ ዛሬም ድረስ በየቦታዉ የሚጠቀምበትን “ክልሉን ለቅቃችሁ ዉጡ” የሚለዉን የዘረኝነት ፓሊሲዉን ገና ከጧቱ በረሃ ዉስጥ እያለ አሳይቶናል።

ወያኔ የትጥቅ ትግል ጀምሮ ጫካ ዉስጥ በቆየባቸዉ ግዜዎች ሁሉ ያሳየዉ ጠባይና አንዳንድ የወሰዳቸዉ እርምጃዎች ዛሬም ድረስ አብዛኛዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ ያጋቡና ዛሬም ድረስ መልስ ያልተኘላቸዉ እንቆቅልሾች ናቸዉ። ለምሳሌ ለህዝብ መብት፤ ነጻነትና እኩልነት እታገላለሁ ባዩ ወያኔ የሱን የመሰለ ተመሳሳይ አላማ የነበራቸዉን ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ህልዉናቸዉ እስኪጠፋ ድረስ በመሳሪያ ጭምር ተፋልሟቸዋል። በወቅቱ መሳሪያ አንግበዉ ለኤርትራ ህዝብ ነጻነት ይታገሉ የነበሩትን ጀብሃንና ከሻዕቢያን በተለይ ሻዕቢያን ግን ልክ እንደፈጣሪዉ ተመልክቶ ለፈጠሪ አምላክ ብቻ የሚሰጠዉን ስግደትና ማደግደግ ለሻዕቢያ ካለምንም ይሉኝታ ሰጥቷል። በትጥቅ ትግሉ ዘመን በነበረዉ የወያኔና የሻዕቢያ ግንኙነት የወያኔ መሪዎች ከሻዕቢያ ጋር ባልተስማሙባቸዉ ግዜዎቸም ቢሆን ወያኔ ሻዕቢያን እንደ ጌታዉ ማየቱንና ለሻዕቢያ መታዘዙን ያቆመበት አንድም ግዜ እንዳልነበረ ዛሬ በወቅቱ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የነበሩ ግለሰቦች በቁጭት የሚናገሩት ሐቅ ነዉ። የወያኔና የሻዕቢያ አላማ ተመሳሳይ እንዳልነበረ ለሁሉም ሰዉ ግልፅ ይመስለናል። ከሁለቱ የለየላቸዉ ከሀዲዎች ከመለስ ዜናዊና ከስብሀት ነጋ ዉጭ የአብዛኛዉ የህወሓት መሪና አባል አላማ የትግራይ ህዝብ መብትና ነጻነት በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ዉስጥ ተከብሮ እንዲኖር ነዉ። የጀብሀና የሻዕቢያ አላማ ግን ከዚህ ፍጹም የተለየ ነበር። ሆኖም ወያኔ ከሱ ጋር ተመሳሳይ አላማ ያላቸዉን ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ድርጅቶች እየወጋ ለየት ያለ አላማ ላለዉ ሻዕቢያ ግን እጁን ሰጥቶ በወዶ ገባነት የኖረ ድርጅት ነዉ። ባጠቃላይ የአገራችን የክርስትና እምነት መሠረት በሆነችዉ ትግራይ ዉስጥ ተወልደዉ ያደጉት የወያኔ መሪዎች ሻዕቢያን እንዳምላካቸዉ ስለሚያዩ አጠጋባቸዉ ካለችዉ አክሱም ፅዮን ይልቅ ኤርትራ ድረስ እየሄዱ ለሻዕቢያ እንደ ታቦት ጎንበስ ብለዉ ሰግደዋል። ዛሬ እነዚህ የሻዕቢያ የእልፍኝ ዉስጥ ተላላኪዎችና ሻዕቢያ እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ ማደጎ ልጅ ያሳደጋቸዉ ከሃዲዎቹ የወያኔ መሪዎች ናቸዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት፤ እከኩልነትና ሰላም የሚታገሉ ድርጅቶችን ከሻዕቢያ ጋር ይሰራሉ እያሉ ክስ የሚያቀርቡት። ደንቆሮዎቹ የወያኔ መሪዎች ምንም ነገር ስለማይገባቸዉ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ እነሱ ሆን ብለዉ በቆፈሩት ጉድጓድ ዉስጥ ገብቶ ቁም ስቅሉን እያየ ነዉ። የዚህ ህዝብ ፍላጎት ከዚህ የምድር ላይ ገሀነም ከሆነ ጉድጓድ ዉስጥ መዉጣት ብቻ ነዉ። በሻዕቢያ በኩል ይዉጣ፤ በኬንያ ወይም በጂቡቲ በወያኔ እሳት የሚለበለበዉ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደዚህ አይነቱን የቅንጦት ምርጫ ለማስተናገድ ግዜም ትዕግስትም የለዉም።

ወያኔ በ1983 ዓም አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ የሽግግር መንግስት ሲያቋቁም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ከሆነባቸዉ ነገሮች አንዱ የሽግግር መንግስቱን የማቋቋሚያ ሂደትም ሆነ በሚቋቋመዉ የሽግግር መንግስት ዉስጥ የሚወሰኑ ዉሳኔዎች ሁሉ በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚወሰኑ ዉሳኔዎች መሆናቸዉን ማረጋገጥ ነበር። ለዚህ ነዉ የትግራይን ህዝብ ሰባትና ስምንት ግዜ እጥፍ የሚበልጠዉን የኦሮሞን ህዝብ እወክላለሁ የሚለዉ ኦነግ ገና ከጥዋቱ የሽግግር መንግስቱን ዘፈንና ጭፈራ ከተመለከተ በኋላ “ከዚህስ ጎመን በጤና” ብሎ ሁለተኛ ዙር የትጥቅ ትግሉን የጀመረዉ። በሽግግር መንግስቱ ዉስጥ ህገመንግቱን ማርቀቅን፤ የፌዴራል ስርዐት ማቋቋምንና የክልል አመሰራረትን ጨምሮ የሽግግር መንግስቱንና ከዚያም በኋላ የተፈጠረዉን የዉሸት መንግስት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ሁሉንም ስራ የሰራዉ ህወሐት ብቻ ነዉ፤ ሌሎቹ ከአጃቢነት ዉጭ ሌላ ምንም አይነት የጎላ ሚና አልነበራቸዉም።

በኢትዮጵያ የሙያ ማህበራት ታሪክ ዉስጥ ረጂም ታሪክና ጉልህ የአስተባባሪነትና የህዝባዊ ትግል መሪነት ሚና የነበራቸዉ ሁለቱ አንጋፋ የሙያ ማህበራት የኢትዮያ ሰራተኞች ማህበር (ኢሰማ) እና የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ነበሩ። እነዚህ ሁለት የሙያ ማህበራት ዛሬም መኖራቸዉ ጥርጥር ዉስጥ እስኪገባ ድረስ ደብዛቸዉ የጠፋዉ ወያኔ ሁለቱንም ማህበራት በቁጥጥሩ ስር በማድረጉ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩ የሲቪክ ማህበራትና የዲሞክራሲ ግንባታ ተቋሞች ከዉጭ አገር ምንጮች እርዳታ እንዳያገኙ በማድረግ እነዚህ ተቋማት ወይ በወያኔ ቁጥጥር ስር እንዲደራጁ አለዚያም እንዲጠፉ አድርጓል። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ እንቅስቃሴያቸዉን ብቻ ሳይሆን ህልዉናቸዉን ጭምር ሙሉ በሙሉ የማይቆጣጠር ምንም አይነት ህዝባዊ ተቋማት ወይም የሙያ ማህበራት የሉም።

ወያኔ ቄስ፤ ሼክ፤ መምህር፤ አሰልጣኝ፤ የአገር መሪ፤ ነጋዴ ወዘተ ሁሉንም ነገር መሆን የሚፈልግ ብቻ ሳይሆን መሆን የማይችለዉን ካልሆንኩ እያለ አገር የሚያበላሽ ችኮ ድርጅት ነዉ። ወያኔ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ከቤ/ክርስቲያን ህግና ደንብ ዉጭ የተሾመ ጳጳስ እያለ የራሱን ታጣቂ ጳጳስ የሾመ ዉግዝ ከመአሪዮስ የሆነ ድርጅት ነዉ። ወያኔ የክርስቲያን ተቋሞችን መቆጣጠሩ አልበቃ ብሎት ፊቱን ወደ መጂሊስ አዞሮ የእስላምና እምነት ተከታዮችንም ከእምነታቸዉ ዉጭ እምነት ካልሰጠኋችሁ ወይም ካልተቆጣጠርኳችሁ እያለ ያስቸገረ እኩይ ድርጅት ነዉ። ዛሬ ወያኔ ከእስልምና እምነት ተከታዮች ጋር የገባዉ ከፍተኛ ቅራኔና በጥቁር ህዝብ ታሪክ ዉስጥ በጥንታዊነቷ የምትታወቀዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ህጋዊዉ ሲኖዶስና የወያኔ ሲኖዶስ ተብላ ለሁለት የተከፈለችዉ ወያኔ የሙስሊሞቹን መጅሊስና እቺን ጥንታዊት ቤ/ክርስቲያን ለመቆጣጠር እጅግ በጣም ፀያፍ የሆነ እርምጃ በመዉሰዱ ነዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ የሐይማኖት ነጻነት ተረጋገጠ ብሎ የነገረን ወያኔ ባጳጳስ ላይ ጳጳስ ሾሞ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን የተቆጣጠረዉ ገና በጧቱ ነበር። ወያኔ ጳጳስ ብሎ የሾማቸዉ የአድዋዉ ተወላጅ አባ ጳዉሎስ ጳጳስ ሆነዉ ባገለገሉባቸዉ አመታት ሁሉ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የጋምቤላው ውጥረት አሁንም እንደቀጠለ ነዉ

ጋምቤላ ዉስጥ አቦቦ በሚባለው አካባቢ የተጀመረውን ግጭት ተከትሎ ወያኔ የሚወስደዉን ፀረ ህዝብ እርምጃ በመቃወም መንግስት ያስታጠቃቸው ከ15 በላይ ታጣቂዎች ስርአቱን አናገለግልም በማለት መጥፋታቸውንና የመከላከያሰራዊት አባላትም ታጣቂዎችን ለመያዝ አሰሳ መጀመራቸውን ጋምቤላ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የመንግስት ታጣቂዎች የነበሩ የጋምቤላ ተወላጆች ከመጥፋታቸው በፊት በመከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ በመወሰዱት እርምጃ ሁለት የመከላከያ አባላት መገደላቸውንና የተወሰኑትም ማቁሰላቸውን ምንጮች ገልጸዋል።

በመዠንገር አካባቢ የተነሳውን ግጭት ለመቆጣጠር መንግስት አሁንም የመከላከያ ሃይሉን በስፋት አሰማርቶ የሚገኝ ሲሆን፣ በመዠንገር ተወላጆች ላይ ጠንካራ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን የመከላከያ ሰራዊትን ዋቢ በማድረግ ወኪላችን ገልጿል። በርካታ ቁጥር ያላቸው የመዠንገር ተወላጆችና የወረዳ አመራሮች መታሰራቸውን የገለጸው ወኪላችን፣ የታሰሩት ተወላጆች የቶር መሳሪያ እንዳልተገኘባቸው አክሎ ተናግሯል። በሌላ በኩል ከ40 ያላነሱ የፌደራል ፖሊሶችና ከ10 በላይ የመከላከያና የወረዳ ታጣቂዎች የተገደሉበትን ግጭት በተመለከተ መረጃ ያካፈሉን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ከ30 በላይ የሚሆኑ የፌደራል ፖሊሶች የተገደሉት በኦራል መኪና ላይ እንዳሉ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት ነው። ጥቃቱን ተከትሎ ታጣቂዎቹ መሳሪያዎችና ከርቀት ማሳያ መነጽሮችን መውሰዳቸውን ነዋሪዎች አክለው ተናግረዋል።

በጋምቤላ ከተማ ላለፉት ሶስት ቀናት የነበረው ውጥረት እየቀነሰ በመምጣጡ ሱቆች መከፈት መጀመራቸውንና የከተማው ህዝብ ከቤት መውጣት መጀመሩን የሚገልጹት ነዋሪዎች ሁኔታው ግን አሁንም አስፈሪ መሆኑን ተናግረዋል። አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በአካባቢው ለሚታየው ግጭት አንዳንድ የአካባቢው ባለስልጣናትንና ተቃዋሚዎችን ተጠያቂ ቢያደርጉም ስለተገደሉት የፌደራል ፖሊሶችና የመከላከያ አባላት ሰይናገሩ ቀርተዋል። አቶ ግርማ ሰይፉም ጉዳዩን በተመለከተ ለጠ/ሚኒስትሩም ጥያቄ አላቀረቡም።

## ሥልጠናዉን ያዘጋጀነዉ ተቃዋሚዎች የሚረጩትን መርዝ ለማርከስ ነዉ - ሃይለማርያም ደሳለኝ

ከ547 መቀመጫዎች ዉስጥ 546ቱን ወያኔ ለብቻዉ ይዞት በሚቆጣጠረዉ ፓርላማ ዉስጥ ብቸኛ የተቃዋሚ ድምጽ የሆኑት አቶ ግርማ ሰይፉ፣ በቅርቡ የወያኔ አገዛዝ ለዩኒቨርስቲ መምህራን፣ ተማሪዎችና የመንግስት ሰራተኞች የሰጠውን የፖለቲካ ስልጠና አስመልክቶ ላቀረቡት ጥያቄ መልስ የሰጠዉ የወያኔዉ ተላላኪ ሃይለማርያም ደሳለኝ፣ ውይይቱን ማድረግ ያስፈለገው ትምክህተኞች፣ ጸረ ሰላም ሃይሎችና ጠባቦች የሚረጩትን መርዝ ትክክል አለመሆኑን ለማሳየት ነው ሲል መመለሱ ተሰማ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግስት ባለስልጣናትና ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን በመጥላታቸው በብሄሮች መካከል መቃቃር እና ግጭቶች እንዲፈጠሩ እየሰሩ በመሆኑ መንግስት በሁለቱም ላይ እርምጃ ይወስዳል ብለዋል።በጋምቤላ በመዠንገር አካባቢ የተከሰተው ግጭት በመንግስት ባለስልጣናትና በተቃዋሚዎች የተፈጠረ መሆኑን፣ እጃቸው አለበት የተባሉ የመንግስት ባለስልጣናት በቁጥጥር ስር ማዋላቸውን ጠ/ሚ ተናግረዋል።

የጠ/ሚንስትሩ ንግግር ኢህአዴግ በየቀኑ እርሱ በሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሃን የሚያሰራጨው ፕሮፓጋንዳ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ እንዳሳሰበው፣ በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው አለመረጋጋት እየጨመረ መምጣቱን ለማመን መገደዱን ያሳየነ ነው ሲል በስፍራው የተገኘው ዘጋቢያችን ገልጿል።

አቶ ግርማ ሰይፉ መንግስት በአምስት አመታት ውስጥ ያቀደውን እቅድ ከፕሮፓጋንዳ ባለፈ በበቂ ሁኔታ ሊሰራ አለመቻሉን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማንሳት ጠይቀዋል። የባቡር መንገድ ከ100 ኪሜትሮች በላይ አለመሰራቱ፣ ይህን ድክመት ለመሸፈንም በአዲስ አበባ ያለውን የባቡር መንግድ ደጋግሞ በማሳየት ድክ መትን ለመሸፈን ሙከራ መደረጉን አቶ ግርማ ገልጸዋል። አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ፣ የባቡር ፕሮጀክቶች በብድር የሚሰሩ በመሆኑን በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ ብድር ለማግኘት ችግር መኖሩን በመጠቆም ትኩረቱ ከአዲስ አበባ ጅቡቲና ከመቀሌ አዋሽ ባሉት የባቡር ፕሮጀክቶች ላይ መሆኑን ገልጸዋል። ይሁን እንጅ እነዚህም ፕሮጀክቶች ከጅምር ያለፉ አለመሆኑን ከንግግራቸው ለመረዳት ተችሎአል።

70 በመቶ የስኳር ፋብሪካዎች በዚህ አመት እንደሚጠናቀቁና ስኳር በማምረት ወደ ውጭ መላክ እንደሚጀመር ጠ/ሚ ቢናገሩም፣ በመላ አገሪቱ ስኳር በመጥፋቱ ሻሂ ቤቶች ስኳር በኮታ ለመውሰድ እየተገደዱ፣ ሌሎች ተጠቃሚዎች በቂ ስኳር ለማግኘት በማይችሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።

ጋዜጠኞች እየታሰሩ፣ የውይይት ምህዳሩ እየጠበበ መምጣቱን የገለጹት አቶ ግርማ፣ መንግስት ከጦር ይልቅ ሃሳብንና ውይይትን እንደሚፈራ ያሳያል ብለዋል። አቶ ሃይለማርያም ጋዜጠኞች ህዝብን ከህዝብ ለማጋሸትና ሽብር ለመፈጸም በመንቀሳቀሳቸው መታሰራቸውን በመግለጽ የአቶ ግርማን አስተያየት ውድቅ አድርገዋል።

## በቤንች ማጅ ዞን በተቀሰቀሰው ጦርነት ከ 115 በላይ ዜጎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለዘመናት የኖሩ ነዋሪዎችን በአስቸኳይ ወረዳዋን ለቀው እንዲወጡ የሚያሳስብ ወረቀት መበተናቸው ታውቋል። በተለይ በርካታ ቁጥር ያላቸው የተፈናቀሉ ኢትዮጵያን በሚዛን ከተማ ጎዳናዎች ተበትነው መጠለያ አጥተው በችግር ላይ እንደሚገኙም ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የጦርነቱ መነሻ ፋሽስቱ ወያኔ በአካባቢው የቀበረው የዘር ፖለቲካ እንደሆነ በስፋት ይነገር እንጂ በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ በአካባቢው በጉጅሌው ወያኔ ቱባ ሹማምንቶችና ቅጥረኛ ባለሃብቶ የተደረገው የመሬት ቅርምት ለችግሩን መባባስ አብይ ምክንያት መሆኑ ተነግሯል። በቅርቡም በጋምቤላ ክልል በጐደሬ ወረዳ የፋሽስቱ ወያኔ ቱባ ሹማምንቶችና ቅጥረኛ ባለሃብቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ዜጐችን በማፈናቀል መሬታቸውን በመቀራመታቸው ተከትሎ የአካባቢው ነዋሪዎች ተቆጥተው በወሰዱት እርምጃ ከፍተኛ እልቂት ፈጥሮ ማለፉን እየተከታተልን መዘገባችን አይዘነጋም። በማፈናቀሉ ሒደት ከ540 በላይ ዜጐች ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት ደግሞ ቤት ንብረታቸውን ጥለው እንዲሰደዱ መደረጉ ይታወሳል:: ፋሽስቱ ወያኔ በመላ አገሪቱ እስካሁኑ በተፈጸሙና አሁንም እየተፈጸሙ በሚገኙት የማፈናቀልና የመግደል ወንጀሎች ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን አገዛዙ ርካሽ የፖለቲካ ጥቅማና የህዝብ ይሁንታ ለማግኘት በተፈጸሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተሳታፊ የነበሩትን ቅጥረኛ ካድሬዎቹን በህግ ቁጥጥር ሥር አውያለሁ የሚል ዲስኩር ሲነዛ እንደነበር አይዘነጋም። ይሁን እንጂ አገዛዙ ምንም አይነት ለህዝብ ይፋ የተደረገ ተግባራዊ እርምጃ በቅጥረኛ ካድሬዎቹ ላይ አለመውሰዱ ይታወቃል። ከዚህ ቀደም በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ተመሳሳይ ድርጊት የፈጸሙትን ቅጥረኛ ካድሬዎቹን በቁጥጥር ስር አውያለሁ ይበል እንጂ የፖለቲካ ፍጆታ ከማድረግ ውጭ ምንም ዓይነት እርምጃ አለመውሰዱ ይታወሳል።

## የዘረኞች ፍርድ ቤት ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የወያኔ አገዛዝ በተለይ በጸረ ሽብር ትግል ስም የሚያስራቸውን የህሊና እስረኞች በአፋጣኝ እንዲፈታ በተደጋጋሚ መጠየቁ ይታወሳል። በእስር ላይ የሚገኙት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ርእዮት አለሙና ውብሸት ታየ የተለያዩ አለማቀፍ ሽልማቶች አሸናፊ መሆናቸው ይታወቃል።

በሌላ ዜና ባሳለፍነው ወር ለስደት ከተዳረጉት 23 ጋዜጠኞች መካከል የማራኪ መፅሔት ባለቤት እና ማኔጂንግ ዳይሬክተር የነበረው ጋዜጠኛ ሚሊዮን ሹሩቤ በስደት በሚኖርበት ናይሮቢ ኬኒያ ሰኞ ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ.ም. በድንገት ህይወቱ ማለፉን ለማወቅ ተችሏል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## “እኔ ብቻ” ቢያክሙት የማይሽር የወያኔ በሽታ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ወገባቸዉን ባጭር ታጥቀዉ ያገለገሉት የሰማዩን አባታቸዉን ሳይሆን የአድዋዉን ወንድማቸዉን መለስ ዜናዊን ነዉ። ፍርድ የማይሳነዉ እግዚአብሄርም ይህንን ምህረት የማይገባዉ በደል ተመልክቶ ነዉ እነዚህን ሁለት አመጸኞች መንፈቅ በማይሞላ ግዜ ዉስጥ ተራ በተራ የወሰዳቸዉ። ወያኔ አይናቸዉ ገንዘብና ንብረት ካየ በፍጹም አርፈዉ የማይተኙ ስግብግቦች ስብሰብ ቢሆንም የኢተዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያንን ይቆጣጠራል ወይም ተቆጣጠረ ስንል ወያኔ የሚቆጣጠረዉ የቤ/ክርስቲያኒቱን ገንዘብና ንብረት አይደለም፤ ይልቁንም ወያኔ በቅርብ የሚቆጣጠረዉ የቤ/ክርስቲያኒቱን ዋና ዋና ዉሳኔዎችና ቤ/ክርስቲያንቱ በማህበረሰቡ ላይ ማድረስ የምትችለዉን ተፅዕኖ ነዉ። ዛሬ ወያኔ “ማህበረ ቅዱሳን” በሚል ስያሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ስር የተደራጁ የእምነታቸዉ ቀናተኞችን ዉስጣችሁ ካልገባሁ እያለ የሚያዉካቸዉ አብሯቸዉ ፈጣሪን ለማምለክ ሳይሆን ያንን ሁሉንም ነገር ካልተቆጣጠርኩ የሚለዉን አባዜዉንና ስስቱን ለማርካት ሲል ብቻ ነዉ።

የሚገርመዉ ወያኔ የኢትዮጵያ ህዝብ ከሱ ቁጥጥር ዉጭ ሲተነፍስም ደስ ስለማይለዉ አንድ ለአምስት የሚባል የኮሚኒስቶች አደረጃጀት ይዞ መጥቶ ወጣቶችን፤ ሴቶችን፤ ሰራተኞችን፤ ገበሬዎችንና መምህራንን በአንድ ለአምስት አደራጅቶ አንዱ ስለሌላዉ በየቀኑ መረጃ እንዲሰበስብና ለበላይ አካላት እንዲያሳዉቅ አድርጓል። ስለሆንም ይህንን የወያኔን “እኔ ብቻ” የሚል አባዜ ከስሩ መንግሎ ለመጣል ብቸኛዉ መንገድ ወያኔን እራሱን በተባበረ ክንድ መንግሎ መጣል ነዉ እንጂ ዋልድባ፤ መጅሊስ፤ ወይም ማህበረ ቅዱሳን እያልን በተናጠል የምናደርገዉ ትግል ዋጋ የለዉም፤ ወይም ወያኔ ወደ እያንዳንዳችን አናት ላይ እስኪወጣ መጠበቅ የለብንም። ወያኔ ሌሎችን ሲያጠቃ “እኛ የለንበትም” ብለን ቁጭ ብለን እየተመለከትን የወያኔ ዱላ እኛጋ ሲደርስ የምናሰማዉ የድረሱልኝ ጩኸት ሰሚ አያገኝም - ማግኘትም የለበትም። የወያኔን ዘረኝነትና “እኔ ብቻ” የሚያሰኝ ክፉ በሽታ ለማጥፋት ብቸኛዉ መንገድ ወያኔንና ስርዐቱን በህዝባዊ ትግል ገርስሶ መጣል ብቻ ነዉ፤ ህዝባዊ ትግል ደግሞ መቀራረብን፤ መከባበርን፤ መተሳሰብን፤ አንድነትንና ትብብርን ይጠይቃል። እንግዲህ እንደ ትናንቱ ሁሉ የዛሬዉም ጥሪያችን ኑና ወያኔን በተባበረ ክንድ እንጣል የሚል ነዉ።